የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፮ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 39
ADDIS ABABA 3rd June, 2014


ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፫፻፮/፪ሺ፮ ዓ.ም.
የሽብርተኛ ሀብት የሚታገድበት ሥነ-ሥርዓት
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...................... ገጽ ፯ሺ፬፻፪


CONTENTS


Regulation No. 306/2014

Procedures for Freezing of Terrorist's Assets Council of Ministers Regulation.............................. Page 7402


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፮/፪ሺ፮

## የሽብርተኛ ሀብት የሚታገድበትን ሥነ-ሥርዓት ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፴፬፣ በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩ አንቀጽ ፴፯ እና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ አንቀጽ ፶፬(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሽብርተኛ ሀብት የሚታገድበት ሥነ-ሥርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፮/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት ወይም ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No 306/2014

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR PROCEDURES FOR THE FREEZING OF TERRORIST'S ASSETS

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010, Article 37 of the Anti-Terrorism Proclamation No.652/2009 and Article 54(1) of the Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No.780/2013.

### PART ONE

### GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Procedures for Freezing of Terrorist's Assets Council of Ministers Regulation No. 306/2014".

**2. Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No.780/2013;


ያንዱ ዋጋ Unit Price 11.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ሥር ለተመለከቱት ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፫/ "ማዕከል" በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፩/፪ሺ፪ የተቋቋመው የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ነው፤

፬/ "ኮሚቴ" ማለት በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፯ (፲፱፻፺፱)፣ ፩ሺ፱፻፹፰ (፪ሺ፲፩)፣ ፩ሺ፱፻፹፱ (፪ሺ፲፩) ወይም አግባብ ባለው ሌላ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት የተቋቋመ ማዕቀብ የሚወስን አካል ነው፤

፭/ "ፍርድ ቤት" ማለት የፌደራል ከፍተኛ ወይም ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፤

፮/ "ኃላፊነት ያለበት ሰው" ማለት ማዕከሉ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ሕግ መሠረት ሥልጣንና ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ለማዕከሉ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ያለበት ሰው ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ) የፋይናንስ ተቋማትን፤

ለ) ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎችን፤

ሐ) ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችንና የሃይማኖት ድርጅቶችን፤

መ) የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን፤

ሠ) የበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ፤ እና

ረ) ሌሎች የማገድ ግዴታ ያለባቸው ወይም በማዕከሉ ሪፖርት እንዲያቀርቡ የተለዩ ሰዎች::

፯/ "አግባብነት ያለው ባለስልጣን" ማለት ማዕከሉ፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ ፖሊስ፣ ዓቃቤ ህግ ወይም የምርመራ ስራን በኃላፊነት የሚሰራ አካል፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ወይም የሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ነው፤

፰/ "የተሰየመ ሰው" ማለት:-

ሀ) በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩ መሠረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት፤

ለ) በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፯/፲፱፻፺፱ ወይም አግባብነት ባለው ማንኛውም የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት ሽብርተኝነትን ለመዋጋት ተለይተው የተቀመጡ የቁጥጥር እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በተመለከቱት የተወሰኑ ሰዎችና ድርጅቶች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ፤ ወይም

2/ the definitions assigned to the terms under Article 2 of the Proclamation shall be applicable;

3/ "Center" means the Financial Intelligence Center established by the Council of Ministers Regulation No. 171/2009;

4/ "Committee" means an organ established pursuant to United Nations Security Council Resolution 1267 (1999), 1988 (2011) or 1989 (2011) or any other relevant Resolution of the United Nations Security Council to impose sanctions;

5/ "Court" means the Federal High or Supreme Court;

6/ "accountable person" means a person who has a duty to report to the Center while exercising its power and functions under the Proclamation, this Regulation or other relevant laws, and includes:

a) financial institutions;

b) designated non-financial businesses and professions;

c) not-for-profit and religious organizations;

d) Ethiopian Revenues and Customs Authority;

e) the Charities and Societies Agency; and

f) other persons with a duty to freeze assets or identified by the Center to submit report to it.

7/ "competent authority" means the Center, National Intelligence and Security Service, the Police, Public Prosecutor, or other investigative body, the Ethiopian Revenues and Customs Authority or any concerned regulatory authority;

8/ "designated person" means an individual, a group or an organization:

a) proscribed by the House of Peoples' Representatives or convicted by court, in accordance with the Anti-Terrorism Proclamation No. 652/2009;

b) included in the list referred to in the United Nations Security Council Resolution No. 1267 (1999) or any other relevant United Nations Security Council Resolution on specific restrictive measures directed against certain persons and organizations with a view to combating terrorism; or

ሐ) በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፫(፪ሺ፩) መሠረት ሥልጣን ባለው የሌላ አገር የመንግስት አካል በአሸባሪነት የተሰየመ፤

ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ነው፡፡

፱/ "የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው" ማለት የሽብርተኝነት ድርጊት ፈፅሞ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጠው ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባለ ሰው ነው፤

፲/ "ሀብት" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፪ እንደተተረጎመው ፈንድ፣ ገንዘብ፣ የኢኮኖሚያዊ ሀብት፣ ንብረት ወይም አገልግሎት ነው፤

፲፩/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፪/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

### ስለተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝርና ስያሜን ስለማሳወቅ

**፫. የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር**

፩/ ማዕከሉ ማንኛውንም የተሰየመን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) በተጠቀሰው አግባብ ያለው ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት ማድረግ አለበት፡፡

፪/ ማዕከሉ የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝሮችን እንደየአግባቡ "የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዝርዝር"፣ "የተባበሩት መንግሥታት ዝርዝር"፣ "የውጭ አገር መንግሥት አካል ዝርዝር" እና "የፍርድ ቤት ዝርዝር" በሚሉ ስያሜዎች ለይቶ ይይዛል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሰረት የተያዘ ዝርዝር የተሰየመን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ማንነት ለመለየት የሚያስችሉ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡ እነዚህም መረጃዎች ሊታወቁ እስከቻሉ ድረስ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ) የተሰየመውን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ስም፣ የቤተዘመድ ስም እና ሌሎች መጠሪያዎችና የማዕረግ ስሞች ካሉ፤

ለ) የተወለደበት ቦታና ቀን ወይም ተቋም ከሆነ የምዝገባ ቁጥሩን ጨምሮ የተመዘገበበትን ቦታና ቀን፤

ሐ) ፆታ፣ ዜግነትና አድራሻ፤

መ) ሙያ፣ ሥራ፣ ወይም የንግድ ሥራ ዓይነት፤

ሠ) ስያሜው ወይም የፍርድ ውሳኔው የተላለፈበት ቀን፤

c) proscribed by a competent foreign jurisdiction and in accordance with United Nations Security Council Resolution Number 1373 (2001).

9/ "convicted person" means one who has committed a terrorist act and found guilty for the same act by the court that rendered a final decision;

10/ "assets" means funds or monies or economic resources or properties or services as defined under Article 2 of the Proclamation;

11/ "person" means a natural or juridical person;

12/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

### LISTS OF DESIGNATED OR CONVICTED PERSONS AND NOTIFICATION OF DESIGNATION OR CONVICTION

**3. Lists of Designated or Convicted Persons**

1/ The Center shall include such individual, group or organization in the appropriate list of designated or convicted persons as categorized pursuant to sub-article (2) of this Article.

2/ The Center shall categorize the lists of designated or convicted persons into "the House of Peoples' Representatives List", "the Court List", "the United Nations List", and "the Foreign Jurisdiction List".

3/ Any list of designated or convicted persons in accordance with sub-article (2) of this Article shall comprise information relating to the person for the purpose of determining his identity. Such information shall include, where known:

a) name of the designated or convicted person, family name and pseudonyms and titles, if any;

b) place and date of birth or if it is an entity, the place and date of registration including the registration number;

c) sex, nationality and address;

d) occupation, job, or type of business;

e) the date of designation or conviction;

ረ) በተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈ ባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተተበት ቀን፣ እና፤

ሰ) የእግድ እርምጃዎችን አፈጻጸም ውጤታማ ለማድረግ አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታመ ንባቸው ሌሎች መረጃዎች::

፬. **የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝሮችን ስለማሰራጨት**

፩/ ማዕከሉ የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለ ፈበትን ሰው ዝርዝር እና የዝርዝሩን ማሻሻያዎች ለሁሉም ኃላፊነት ላለባቸው ሰዎችና ለሚመለከ ታቸው የመንግስት አካላት ሳያዘገይ ማሰራጨት አለበት፤ እንደአስፈላጊነቱም ለህዝብ ግልፅ ያደርጋል::

፪/ ማዕከሉ ስለተሰየሙና የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባ ቸውን ሰዎች በዚህ ደንብ መሠረት የሚፈለጉ መረጃዎችን ሲጠየቅ ለሚመለከተው ሰው ይሰጣል::

፫/ ማዕከሉ የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈ በትን ሰው በዚህ ደንብ አንቀፅ ፰(፪) መሠረት ሃብቱ እንዲታገድ ካደረገ በኋላ የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎችን ዝርዝር ለህዝብ ይፋ ያደርጋል::

፭. **መሰየምን ወይም የፍርድ ውሳኔ መተላለፍን ስለማሳወቅ**

፩/ ማዕከሉ የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለ ፈበት ሰውን ሃብት እንዲታገድ ካደረገ በኋላ ይህ ሰው የኢትዮጵያ ዜጋ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ በተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት የተደረገበትን ምክንያት እና ከዝርዝሩ ሊሰረዝ የሚ ችልበትን ሥነ-ሥርዓት በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት::

፪/ በመሰየሙ ወይም በፍርድ ውሳኔ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር ማዕከሉ በዚህ ደንብ አንቀፅ ፲፪ መሰረት የታገደ ሀብት ክፊሉን መጠቀም ስለ ሚቻልበት ሁኔታ እና ስነ- ስርዓት ለተሰየመው ሰው በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት::

፮. **የመሰየም ወይም የፍርድ ውሳኔ ዝርዝርን መሠረዝ ወይም ማሻሻል**

የመሰየም ወይም የፍርድ ውሳኔ እንደነገሩ ሁኔታ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በኮሚቴው ፣ሥልጣን ባለው የውጭ አገር መንግሥት አካል ወይም በፍርድ ቤት የተሠረዘ ወይም የተሻሻለ እንደሆነ ማዕከሉ ወቅታዊነቱን በጠበቀ ሁኔታ የሚከተሉትን መፈጸም አለበት፡-

f) date of inclusion of name of the list of designated or convicted persons ; and

g) any other information as may be considered relevant for effective implementation of freezing measures.

4. **Dissemination of Lists of Designated or Convicted Persons**

1/ The Center shall disseminate the lists of designated or convicted persons and any amendments to or delisting from the lists to all accountable persons and the relevant authorities without delay.

2/ The Center shall, on request by any interested person, provide information as may be required under this Regulation with respect to designated persons.

3/ The Center shall disseminate the lists of designated or convicted persons and any amendments to or delisting from the lists to the public after it has frozen the assets pursuant to Article 8(2) of this Regulation.

5. **Notification of Designation or Conviction**

1/ The Center shall make every effort to give prompt and written notification of the designation or conviction, after the freeze of assets has been effected, to the designated or convicted person if he be a national of or located in Ethiopia, providing explanations for the inclusion in the list of designated or convicted persons and advising on procedures for requesting consideration for delisting.

2/ The Center shall, unless otherwise provided in the proscription or conviction, inform a designated person about the possibility of utilizing part of the frozen assets and the procedure thereof in accordance with the provisions of Article 12 of this Regulation.

6. **Revocation or Variation of Designation or Conviction**

Where a designation or conviction has been revoked or varied by the House of Peoples' Representatives, the Court, the Committee or the competent foreign jurisdiction, as the case may be, the Center shall, in a timely manner:

፩/ የተሰየመውን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ስም ከሚመለከተው የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ማውጣት ወይም ዝርዝሩን እንደውሳኔው ማሻሻል፤

፪/ የመሰየም ወይም የፍርድ ውሳኔው መሰረዙን ወይም መሻሻሉን እና የሚያስከትለውን ውጤት ለተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ ለተላለፈበት ሰው በጽሑፍ ማሳወቅ፤

፫/ ስያሜውን እንዲያውቁት የተደረጉ ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎችና የመንግስት አካላት የመሰየም ወይም የፍርድ ውሳኔውን መሰረዝ ወይም መሻሻል እና የሚያስከትለውን ውጤት በፅሁፍ ማሳወቅ፤ እና

፬/ እንደ አግባብነቱ በኮሚቴው ወይም ሥልጣን ባለው የውጭ አገር የመንግሥት አካል የማሻሻል ወይም የመሰረዝ ውሳኔ በተሰጠባቸውና ቀደም ሲል የሀብት ማገድን ጨምሮ በዚህ ደንብ መሰረት የተወሰዱ አስፈላጊ እርምጃዎችን ሁኔታ ለእነዚሁ አካላት በፅሁፍ የማሳወቅ።

፯. **ከተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ለመሰረዝ ስለሚቀርብ ማመልከቻ**

፩/ ስሙ ከተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ ከተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲሰረዝለት የሚፈልግ ሰው፦

ሀ) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ዝርዝር የሚመለከት ሲሆን ማመልከቻውን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ፤

ለ) የፍርድ ቤትን ዝርዝር የሚመለከት ሲሆን ማመልከቻውን የመጨረሻ ውሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት ማቅረብ፤

ሐ) የተባበሩት መንግሥታትን ዝርዝር ወይም የውጭ አገር መንግሥት አካልን ዝርዝር የሚመለከት ሲሆን ማመልከቻውን በማዕከሉ አማካይነት ለኮሚቴው ወይም ሥልጣን ላለው የውጭ አገር መንግሥት አካል ፤

ይችላል።

፪/ ማዕከሉ አንድ የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ክሞተ ወይም ህጋዊ ሰውነቱን ያጣ ከሆነ እና ከተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ ከተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ለመሰረዝ የሚያስችል በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምን እንደ ሁኔታው የዚህን ሰው ስምና ሌሎች ዝርዝሮች ውሳኔውን ለሰጠው አካል ወይም የፍርድ ውሳኔውን ያስተላለፈውን ፍርድ ቤት ፈቃድ ጠይቆ ሲያገኝ ከዝርዝር እንዲሰረዝ ያደርጋል።

1/ remove the name of a designated or convicted person from the relevant list of designated or convicted persons or amend the list accordingly;

2/ give written notice of the revocation or variation, together with its effect, to the designated or convicted person;

3/ take such steps as it considers necessary to bring the revocation or variation, together with its effect, to the attention of the accountable persons and authorities informed of the designation or conviction; and

4/ take appropriate measures to notify the Committee or the competent foreign jurisdiction, as the case may be, of measures taken by it under this Regulation including any measure to freeze assets or the inclusion or deletion of names in or from the list of designated or convicted persons in addition to any steps or actions taken to respond to any direction or request made by the Committee or the competent foreign jurisdiction.

7. **Application for Deletion from the List of Designated or Convicted Persons**

1/ A designated or convicted person who wishes to have his name deleted from the list of designated or convicted persons may, in respect to:

a) the House of Peoples' Representatives List, submit his application through the Center to the House of Peoples' Representatives;

b) the Court List, submit his application to the Court that convicted him;

c) the United Nation List or the Foreign Jurisdiction List, submit his application through the Center to the Committee or the competent foreign jurisdiction.

2/ Where the Center reasonably believes that a designated or convicted person is deceased or is no longer in existence, it shall delete the name and other details of the designated or convicted person upon requesting and obtaining the authorization of the House of Peoples' Representatives, the Court, the Committee or the competent foreign jurisdiction, as the case may be.

## ክፍል ሦስት

## የመሰየም ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ ውጤት

### ፰. ሀብትን ስለማገድ

፩/ ስሙ በተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ውስጥ በሚታይ ሰው ባለቤትነት፣ ይዞታ ወይም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ቁጥጥር ሥር ያለ ሀብት ሳይዘገይ መታገድ አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የተሰየመ ሰው ስም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ መሠረት በተሰየሙ ሰዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት ማድረግን በሚመለከት በአዋጁ አንቀጽ ፴፯ መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በተሰየመው ሰው ባለቤትነት፣ ይዞታ ወይም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ቁጥጥር ሥር ያለ ሀብት ሳይዘገይ በማዕከሉ ውሳኔ መታገድ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ሀብት በማዕከሉ ከታገደ፣ ማዕከሉ ለዚህ ደንብ አንቀፅ ፳፫ አፈፃፀም የሀብቱን መታገድ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት በማዕከሉ ውሳኔ የታገደ ሀብት ስለመኖሩ ማዕከሉ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፭/ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) መሠረት የታገደ ሀብት በይዞታው ሥር የሚገኝ ማንኛውም ሰው የፋይናንስ አገልግሎት መስጠትን ጨምሮ የተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው በሀብቱ እንዳይጠቀም ወይም በዚህ ሰው ስም ጥቅም ላይ እንዳይውል መከልከል አለበት፡፡

፮/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ዓላማ "መጠቀም" ማለት የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) ፈንድን በሚመለከት፡-

(፩) መለወጥን፣ ማንቀሳቀስን፣ ተደራሽነት እንዲኖር መፍቀድን ወይም ማዛወርን፤

(፪) ብዛትን፣ መጠንን፣ የመገኛ አድራሻን፣ ባለቤትነትን፣ ተጠቃሚ የሚሆን ባለቤትነትን፣ ይዞታን፣ ባህሪን ወይም መዳረሻ ቦታን መቀየር በሚችል አግባብ ማናቸውንም እርምጃ መውሰድን፤ ወይም

## PART THREE

## EFFECT OF DESIGNATION OR CONVICTION

### 8. Freezing of Assets

1/ The assets owned, held or controlled, directly or indirectly by a designated or convicted person whose name appears on the list of designated or convicted persons shall be frozen by the Center without delay.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the assets owned, held or controlled, directly or indirectly by a designated person shall be frozen without delay by the decision of the Center until the Council of Ministers decides on the inclusion of the name of the designated person in the list of designated persons pursuant to Article 37 of the Proclamation and Article 3 of this Regulation.

3/ If assets of a convicted person are frozen in accordance with sub-article (1) of this Article, the Center shall notify without delay the same to the concerned authority for the proper enforcement of Article 23 of this Regulation.

4/ Assets frozen pursuant to sub-article (2) of this Article shall be notified without delay to the Council of Ministers.

5/ Subject to Article 11 of this Regulation any person holding any assets frozen pursuant to sub-article (1), (2) or (3) of this Article, shall prevent the use of such assets by or on behalf of the designated or convicted person including the provision of financial services.

6/ For the purpose of sub-article (3) of this Article, "use" shall include:

a) in relation to funds:

(1) alter, move, allow access to, or transfer;

(2) deal with in any other way that would result in any change in volume, amount, location, ownership, beneficial ownership, possession, character or destination; or

(፫) የፖርትፎሊዮ አስተዳደርን ጨምሮ በጥቅም ላይ ማዋልን የሚያስችል ማንኛውንም ሌላ ለውጥ ማድረግን፤

ለ) ኢኮኖሚያዊ ሀብትን በሚመለከት ለግብይት ማዋል ወይም በፈንዶች፣ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መለወጥ፡፡

፯/ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ማንኛውም ሀብት በተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ሥር መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ የሀብቱ ማህበርተኛ በሆነ ወይም ግንኙነት ባለው ሌላ ሰው ስም መያዝ ለውጥ አያመጣም፤ የሽብርተኝነት ድርጊቱ በልዩ ሁኔታ ወይም በጠቅላላው መፈፀሙ እርምጃውን አያስቀረውም፡፡

፰/ ማዕከሉ፡-

ሀ) ለትክክለኛ አስተዳደር እንዲያመች በዚህ ደንብ መሠረት የታገዱ ሀብቶችን በሙሉ በባለቤቶቹ ወይም ተጠቃሚ በሚሆኑት ባለቤቶች ስም መዝግቦ መያዝ አለበት፤

ለ) መመሪያ በማውጣት በዚህ ደንብ መሠረት የታገዱ ሀብቶች የሚተዳደሩበትን ሥርዓት ሊወስን ይችላል፡፡

፱/ በዚህ አንቀፅ መሰረት የተገለጸው የስያሜ ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ ውጤት እንደተጠበቀ ሆኖ ስለጉዞ እና ቪዛ መስጠትን ስለመከልከልና ማገድ፣ የጦር መሳሪያ አቅርቦትና ግዥ ለመፈፀም ወይም የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎች የውትድርና ልምምድ እንዳያደርጉ ስለሚከለክሉ እና ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ማንኛውም አይነት ግብይቶች እና ድርድሮችን ለመከልከል የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው የአገሪቱ ህጎች፣ አለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሚመለከታቸው በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት የተላለፉ ውሳኔዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፱. **<u>የተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው ሰዎችን ዝርዝር ስለመመልከት እና ለማዕከሉ ሪፖርት ስለማድረግ</u>**

፩/ ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት ሰው ከማንኛውም ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ጋር ማናቸውንም ግብይት ከመፈጸሙ ወይም ማናቸውንም ግንኙነት ከመመሥረቱ በፊት የግለሰቡ፣ የቡድኑ ወይም የድርጅቱ ስም በዝርዝሮቹ ውስጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን፣ የተባበሩት መንግሥታትን እና የውጭ መንግሥት አካልን እና የፍርድ ቤትን ዝርዝሮች መመልከት አለበት፡፡

(3) make any other change that would enable use, including portfolio management;

b) in relation to economic resources, exchange or use in exchange for funds, goods or services.

7/ For the purpose of this Article, in determining whether any asset is owned or controlled by a designated person, the fact that such assets are held in the name of an associate or relative will be considered immaterial; and it is immaterial whether the acts of terrorism in question are specific acts of terrorism or acts of terrorism generally.

8/ The Center:

a) shall record all assets frozen under this Regulation against the names of the owners and beneficial owners for proper management;

b) may, by issuing directive, decide the procedure of managing frozen assets under this Regulation.

9/ In addition to the effects of designation or conviction mentioned under this Article, relevant laws of the country, the United Nations Security Council Resolutions and in any subsequent Resolutions in respect of designated or convicted person, and international agreements shall be applicable in respect of prohibition and restriction of travel, the issuance of visas, and purchase of arms, prohibition of transactions or dealings for the supply of arms to or the conduct of military training or other prohibitions for designated or convicted persons.

9. **<u>Reference to Lists of Designated or Convicted Persons and Reporting to the Center</u>**

1/ Any accountable person shall refer to the House of Peoples' Representatives List, the Court List, the United Nations List and the Foreign Jurisdiction List prior to conducting any transaction or entering into any relationship with any individual, group or organization to ascertain whether or not the name of such an individual, a group or an organization is on the Lists.

፪/ የግለሰብ፣ የቡድን ወይም የድርጅት ስም በተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር ውስጥ መኖሩ ሲረጋገጥ፣ ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት ሰው የግለሰቡ፣ የቡድኑ ወይም የድርጅቱ ሀብት መሆኑ ወይም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠረው መሆኑ የታወቀን ሀብት ካገደና ሂሳቡ እንዳይንቀሳቀስ ካደረገ በኋላ ሀብቱን ለማገድ የተወሰዱ ሁሉንም እርምጃዎች የሚመለከቱ መረጃዎችን ጨምሮ "ጥርጣሬ ያለበት ግብይት" በማለት ለማዕከሉ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሰረት ማዕከሉ ሪፖ ርት የቀረበለት እንደሆነ ይህንኑ በአዋጁ መሠረት የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ተጨ ማሪ እርምጃዎችን መውሰድ እንዲችሉ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ኃላፊነት ባለበት ሰው የሚቀርብ ሪፖርት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

ሀ) ሁኔታውን ለማወቅ ወይም ለመጠርጠር መነሻ የሆነውን መረጃ ወይም ሌላ ጉዳይ፤

ለ) የተባለውን ሰው ማንነት ለመለየት የሚያስ ችል ያለውን መረጃ፤

ሐ) ከስያሜው ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ባሉት አሥር ዓመታት ውስጥ ለተባለው ሰው ይዞት የነበረውን ሀብት ዓይነት፣ ባህሪ፣ መጠን እና ብዛት፡፡

፭/ ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፫ መሠረት ወደ ታገደ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ግብይትን ወዲያውኑ ለማዕከሉ ማሳወቅ አለበት፡፡ ማዕከሉም በአዋጁ መሠረት ለሚመለከ ታቸው ባለሥልጣናት ይህንኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

<u>፲. የታገደ ሀብት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደራሽ ስለማድረግ</u>

፩/ በማዕከሉ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት ሰው ሀብትን ለተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ ለተላለፈበት ሰው ወይም ለዚሁ ሰው ጠቀሜታ ለሚያውል ለሌላ ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ የለበትም፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ፡-

ሀ) ሀብት ለተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ ለተላለ ፈበት ሰው ጠቀሜታ እንዲውል ተደራሽ ተደ ረገ ሊባል የሚችለው ይኸው ሰው የፋይናንስ ጥቅም ያገኘበት ወይም ሊያገኝበት የሚችል ሲሆን ነው፤

ለ) የፋይናንስ ጥቅም ሲባልም የተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በኃላፊነት የሚጠየቅበትን የፋይ ናንስ ግዴታ መወጣትንም ይጨምራል፡፡



2/ Where the name of an individual, a group or an organization is confirmed to be on any list of designated or convicted persons, any accountable person shall freeze the assets identified as belonging to or controlled directly or indirectly by such an individual, a group or an organization and shall ensure that the account is rendered inoperable and thereafter forward to the Center a "suspicious transaction report" including information on all actions taken to freeze the assets.

3/ Where the Center obtained information pursuant to sub-article (2) of this Article, it shall in turn in accordance with the Proclamation make a report without delay to the competent authorities for further action.

4/ A report provided by any accountable person in accordance with sub-article (2) of this Article shall include:

a) the information or other matter on which the knowledge or suspicion is based;

b) any information it holds about the person by which the person can be identified;

c) the type, nature, amount and quantity of any asset held by it for the person at any time up to 10 years prior to the designation or conviction.

5/ Where any accountable person credits a frozen account in accordance with Article 13 of this Regulation, it shall promptly report the transaction to the Center. And the Center shall inform the competent authorities in accordance with the Proclamation.

**10. <u>Making Frozen Assets Available to or for the Benefit of a Designated or Convicted Person</u>**

1/ Any accountable person may not make assets directly or indirectly available to a designated or convicted person or to any person for the benefit of such person, unless authorized by the Center.

2/ For the purpose of sub-article (1) of this Article:

a) assets are made available for the benefit of a designated or convicted person only if that person thereby obtains, or is able to obtain, a financial benefit;

b) financial benefit includes the discharge of a financial obligation for which the designated or convicted person is wholly or partly responsible.

## ፲፩. በታገደ ሀብት መጠቀምን ስለመፍቀድ

፩/ የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው በተመለከተ በወንጀል ህግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተሰየመ ሰው መሠረታዊ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልግ ሀብትን የሚመለከት እግድ በማዕከሉ ሲፈቀድና እንደሁኔታው አግባብነት ባለው የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ወይም አግባብ ባለው ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ሊነሳ ይችላል፡፡ እነዚህም መሠረታዊ ወጪዎች እንደነገሩ ሁኔታ የሚከተሉትን ሊጨምሩ ይችላሉ፡-

ሀ) የምግብ፣ የኪራይ ወይም የሞርጌጅ፣ የመድኃኒትና የሕክምና፣ የግብር፣ የኢንሹራንስ አረቦን እና ሌሎች በማዕከሉ የጸደቁ መሠረታዊ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚፈጸሙ ክፍያዎች፤

ለ) የሕዝባዊ አገልግሎቶች ክፍያዎች ወይም የሕግ አገልግሎት ከመስጠት ጋር የተያያዙ ተገቢ ሙያዊ ክፍያዎችንና የወጪ ተመላሾችን ለመሸፈን ብቻ የሚፈጸሙ ክፍያዎች፣ ለታገደ ሀብት መደበኛ አያያዝ ወይም እንክብካቤ ሲባል የሚፈጸሙ የባንክ ወይም የአገልግሎት ክፍያዎች፤ እና

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ያልተካተቱ ሌሎች ልዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚደረጉ ክፍያዎች፡፡

፪/ ከተለመደው በላይ ለሆኑ ወጪዎች የሚያስፈልግ ሀብትን የሚመለከት እግድ የሚነሳው ማዕከሉ ለኮሚቴው አሳውቆት ኮሚቴውም ያፀደቀው እንደሆነ ነው፡፡

## ፲፪. የታገደ ሀብት መጠቀምን የመፍቀድ ሥነ-ሥርዓት

፩/ በዚህ ደንብ አንቀፅ ፲፩ መሠረት የታገደ ሀብትን ለመጠቀም የሚቀርብ ማመልከቻ በተሰየመው ሰው ወይም የውክልና ሥልጣን በተሰጠው ወኪል አማካይነት ከደጋፊ ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች ጋር ለማዕከሉ መቅረብ አለበት፤ ማዕከሉም በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያረጋግጥ በታገደ ሀብት መጠቀምን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፪/ የተሰየመው ሰው በተባበሩት መንግሥታት ወይም የውጭ አገር መንግሥት አካል ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ከሆነ ማዕከሉ የታገደን ሀብት ወይም የሀብቱን ማናቸውም ክፍል ለመጠቀም መፍቀድ ማሰቡን ለሚመለከተው ኮሚቴ ወይም የውጭ አገር መንግሥት አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

## 11. Approval for the Utilization of Frozen Assets

1/ Without prejudice to the provisions of the Criminal Code and other relevant laws with respect to the convicted person, assets that are necessary for the designated person to meet basic expenses may be unfrozen as properly authorized by the Center and in accordance with the provisions set out in the relevant United Nations Security Council Resolution or other laws as appropriate. Such basic expenses, in particular, include:

a) payments for foodstuffs, rent or mortgage, medicines and medical treatment, taxes, insurance premiums and such other basic expenses as the Center may approve;

b) public utility charges, exclusively for payment of reasonable professional fees and reimbursement of incurred expenses associated with the provision of legal services, bank fees or service charges for routine holding or maintenance of frozen assets; and

c) payments for any other exceptional services not provided for in paragraphs (a) and (b) of this sub-article.

2/ Assets that are necessary for extraordinary expenses may be unfrozen provided that such determination has been notified by the Center to the Committee and has been approved by the Committee.

## 12. Procedure of Approval for Utilization of Frozen Assets

1/ Any application to utilize frozen assets under Article 11 of this Regulation shall be made to the Center by the designated person or his authorized representative with supporting documents or evidences. The Center may approve the utilization of frozen assets where it proved the existence of sufficient reason.

2/ In the case of a designated person on the United Nations List or Foreign Jurisdiction List, the Center shall inform the relevant Committee or foreign jurisdiction of its intention to approve the utilization of the frozen assets or any part thereof.

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሰረት በማዕከሉ ሐሳብ የቀረበለት ኮሚቴ ወይም የውጭ ሀገር የመንግሥት አካል በሐሳቡ መስማማቱን ወይም አለመስማማቱን በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ካላሳወቀ የታገደው ሀብት ማዕከሉ በፈቀደው መሠረት በጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

፬/ ኃላፊነት ያለበት ሰው ወይም የታገደው ሀብት ጠባቂ የሆነው ሌላ ወገን የተሰጠውን የመጠቀም ፈቃድ በሥራ ላይ እንዲያውል ፈቃዱ በተሰጠ በ፵፰ ሰዓታት ውስጥ በጽሑፍ እንዲያውቀው መደረግ እና እርሱም ስለተወሰደው እርምጃ በጽሑፍ ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

፭/ በማናቸውም የተሰየሙ ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ የተሰየመ ሰው ወይም ወኪሉ ማመልከቻው ተቀባይነት ማግኘቱን ወይም ውድቅ መደረጉን በሚመለከት በጽሑፍ እንዲያውቀው መደረግ አለበት።

**፲፫. ተጨማሪ ገንዘብን ወደ ታገደ ሂሳብ ገቢ ስለማስገባት**

፩/ የታገደ ሂሳብ የገቢ ምንጭ የሆነ ማንኛውም መጠን ያለው ገንዘብ፡-

ሀ) ከሂሳቡ የመነጩ የወለድ ወይም ሌሎች ገቢዎችን፣

ለ) ሂሳቡ ከመታገዱ በፊት በተደረጉ ውሎች ወይም ስምምነቶች ወይም በተፈጠሩ ግዴታዎች መሠረት የተገኙ ክፍያዎችን፣ እና

ሐ) ወደ ታገደው ሂሳብ የተላለፉ ገንዘቦችን፣

ጨምሮ ወደ ታገደው ሂሳብ ገቢ ተደርጎ የታገደው ፈንድ አካል ይደረጋል፤ ኃላፊነት ያለበት ሰውም እንደዚህ ያለውን ተጨማሪ ገንዘብ መቀበሉን የሚመለከት ሪፖርት ለማዕከሉ ማቅረብ አለበት።

፪/ በዚህ ደንብ የተደነገጉ ክልከላዎችና እርምጃዎች ወደ ታገደው ሂሳብ ገቢ የተደረገውን ተጨማሪ ገንዘብ በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፫/ በዚህ አንቀጽ በተመለከተው መሠረት የተገኘን ፈንድ በመቀበል ገቢ የሚደረግበት ቀደም ሲል የተከፈተ ሂሳብ በሌለበት ሁኔታ መወሰድ ስላለበት አግባብ ያለው እርምጃ ማዕከሉን ማሳወቅ አለበት።

፬/ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "የታገደ ሂሳብ" ማለት በዚህ ደንብ የተደነገጉ ክልከላዎችና እርምጃዎች ተፈጻሚ የሚደረጉበት ኃላፊነት ባለበት ሰው ዘንድ በሚገኝና በተሰየመ ሰው ስም በተከፈተ ወይም የተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በሚቆጣጠረው ሂሳብ የተያዘ ገንዘብ ወይም ኢኮኖሚያዊ ሀብት ነው።

3/ Where such Committee or foreign jurisdiction fails to communicate its endorsement or rejection under sub-article (2) of this Article within 5 working days, the frozen assets may be utilized as approved by the Center.

4/ The accountable person or any other party in custody of the frozen assets shall be informed in writing within 48 hours from the time of approval to implement the approval and furnish a report of the action taken in writing to the Center.

5/ A designated person on any of the lists of designated persons or his representative shall be entitled to be informed of the approval or rejection of his application in writing.

**13. Receipt of Additional Funds into Frozen Accounts**

1/ Any sum of funds accruing to the frozen account, including:

a) interests or other earnings due on the account;

b) payments due under contracts, agreements or obligations that were concluded or arose before the account became a frozen account; and

c) funds transferred to the account;

shall be received and credited into the frozen account and shall constitute part of the frozen funds and the accountable person shall file a report of the receipt of such additional funds with the Center.

2/ The additional funds credited to the frozen account shall be subject to the prohibitions and measures provided under this Regulation.

3/ Where there is no existing account for the receipt of funds as provided under this Article, the accountable person shall inform the Center for appropriate action to be taken in such respect.

4/ For the purpose of this Article, "frozen account" means funds or other economic resources affected by the prohibitions and measures under this Regulation held in an account with an accountable person by or under the direct or indirect control of a designated or convicted person.

## ፲፬. በስህተት ስለታገደ ሀብት

፩/ በስም ተመሳሳይነት በተሰየሙ ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈባቸው ሰዎች ዝርዝር ወይም ሂሳብ ውስጥ በስህተት በማካተት ወይም በሌላ ስህተት ምክንያት ሀብት የታገደ እንደሆነ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው እገዳው እንዲነሳለት ለማዕከሉ ማመልከት ይችላል፡፡

፪/ ማዕከሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ማመልከቻ ከተቀበለ በኋላ ማመልከቻው፡-

ሀ) የተባበሩት መንግስታትን ዝርዝር ወይም የውጭ አገር መንግስት አካልን ዝርዝር የሚመለከት ሆኖ ከተገኘ ማመልከቻውን ከተቀበለበት ቀን አንስቶ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ከሚመለከተው ኮሚቴ ወይም ሥልጣን ያለው የውጭ አገር መንግሥት አካል ጋር ተወያይቶ ውሳኔ ማስተላለፍ አለበት፤

ለ) ስያሜው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ዝርዝር ወይም የፍርድ ቤትን ዝርዝር የሚመለከት ሆኖ ከተገኘ ማመልከቻውን ከተቀበለበት ቀን አንስቶ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ከሚመለከተው ጋር ተወያይቶ ውሳኔ ማስተላለፍ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሰረት የተወሰነውን ውሳኔ ማዕከሉ እንደአግባብነቱ ለአመልካቹ፣ ለሁሉም ኃላፊነት ላለባቸው ሰዎችና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ስለመረጃና ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

## ፲፭. ኃላፊነት ያለበት ሰው ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

፩/ ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት ሰው የሚመለከተው ሰው፡-

ሀ) የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት መሆኑን፤ ወይም

ለ) በአዋጁ መሠረት ወንጀል የፈፀመ መሆኑን፤

ያወቀ ወይም የተጠራጠረ እንደሆነ ይህንኑ ለማዕከሉ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ "የሚመለከተው ሰው" ማለት፡-

ሀ) ኃላፊነት ያለበት ሰው ደንበኛ፤

ለ) ከተሰየመበት ወይም የፍርድ ውሳኔ ከተላለፈበት ቀን በፊት ባሉት አስር ዓመታት ውስጥ በማናቸውም ጊዜ ኃላፊነት ያለበት ሰው ደንበኛ የነበረ፤ ወይም

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ኃላፊነት ካለበት ሰው ጋር ማንኛውንም የሥራ ግንኙነት ያደረገ፤

ሰው ነው፡፡

## 14. Assets Frozen in Error

1/ Where assets are frozen as a result of similarity in names or wrong entries in any of the lists of designated or convicted persons or in the account of a designated person, or as a result of any other error, the person affected may apply to the Center to unfreeze the assets.

2/ Upon the receipt of the application referred to in sub-article (1) of this Article, the Center shall, where the application relates to:

a) the United Nations List or the Foreign Jurisdiction List, make a decision no later than 15 working days from the date of receipt after consultation with the relevant Committee or foreign jurisdiction;

b) the House of Peoples' Representatives List or the Court List, make a decision not later than 15 working days from the date of receipt of the application.

3/ The Center shall inform, in writing, the applicant all accountable persons and the relevant authorities of any decision made under sub-article (2) of this Article.

## PART FOUR

## INFORMATION AND REPORTING OBLIGATIONS

## 15. Reporting Obligations of Accountable Persons

1/ Any accountable person shall inform the Center as soon as practicable if it knows or suspects that a relevant person:

a) is a designated or convicted person; or

b) has committed an offence under the Proclamation.

2/ For the purpose of sub-article (1) of this Article, a "relevant person" means:

a) a person who is a customer of the accountable person;

b) a person who was a customer of the accountable person at any time in the period of ten years immediately preceding the date designation or conviction; or

c) a person with whom the accountable person has had dealings in the course of its business during the period referred to in paragraph (b) of this sub-article.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ሪፖርት የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡-

ሀ) ጥርጣሬው ወይም ማረጋገጫው መሠረት ያደረገውን መረጃ ወይም ሌሎች ማስረጃዎች፤

ለ) የሚመለከተውን ሰው ማንነት የሚገልጽ በእጁ የሚገኘውን ማንኛውንም መረጃ፤ እና

ሐ) ስያሜው ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔው ከመሰ ጠቱ በፊት ባሉት አስር ዓመታት ውስጥ ባለው ማናቸውም ጊዜ ለተሰየመው ሰው ኃላፊነት ባለበት ሰው የተያዘ ማንኛውም ሀብት ዓይነት፣ ባህሪ፣ መጠን እና ብዛት፡፡

## ፲፮. መረጃን የመጠየቅ ስልጣን

፩/ ማዕከሉ የተሰየመን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ወይም ማንኛውንም ኃላፊነት ያለበት ሰው፡-

ሀ) በተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው ወይም እርሱን በመወከል በባለቤትነት ወይም በይዞታነት የተያዘ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ሀብት ስለመኖሩ፤ ወይም

ለ) ስያሜው ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔው ከመሰ ጠቱ በፊትም ሆነ በኋላ የተወገደ ማንኛውም ሀብት ስለመኖሩ፤

ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፪/ ማዕከሉ ከሥራው ጋር በተያያዘ በቂ ምክንያት ያስፈልጉኛል የሚላቸውን የሚከተሉትን ወጪዎች የሚመለከት መረጃ ከተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ ከተላለፈበት ወይም ከማንኛውም ኃላፊነት ካለበት ሰው ሊጠይቅ ይችላል፡-

ሀ) በተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈ በት ሰው ወይም ይህንኑ ሰው በመወከል የተደረጉ ወጪዎችን፤ ወይም

ለ) ለተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ ለተላለፈ በት ሰው ጥቅም ሲባል የተደረጉ ወጪዎችን፡፡

፫/ ማዕከሉ ከሥራው ጋር በተያያዘ በቂ ምክንያት ለሚከተሉት ዓላማዎች የሚፈልገውን መረጃ ማንኛውም በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ የሚገኝ ወይም ነዋሪ የሆነ ሰው እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡-

ሀ) የዚህ ደንብ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ፤

ለ) በአዋጁ ላይ የተመለከተ ወንጀልን ከመፈጸም ጋር የተያያዙ ማስረጃዎችን ለማግኘት፤

ሐ) የሚከተሉትን ለማረጋገጥ፡-

3/ The report to be made pursuant to sub-article (1) of this Article shall state the following:

a) the information or other material on which the knowledge or suspicion is based;

b) any information it holds about the relevant person by which the person can be identified; and

c) the type, nature, amount and quantity of any asset held by the accountable person for the relevant person at any time up to ten years prior to the designation or conviction.

## 16. Power to Request Information

1/ The Center may request a designated or convicted person or any accountable person to provide information concerning:

a) assets owned, held or controlled by or on behalf of the designated or convicted person; or

b) any disposal of assets, whether the disposal occurred before or after the person became a designated or convicted person.

2/ The Center may request a designated or convicted person or any accountable person to provide such information as it may reasonably require about expenditure:

a) by or on behalf of the designated or convicted person; or

b) for the benefit of the designated or convicted person.

3/ The Center may request any person in or resident in Ethiopia to provide such information as it may reasonably require for the purpose of:

a) monitoring compliance with or detecting evasion of this Regulation;

b) obtaining evidence of the commission of an offence under the Proclamation;

c) establishing:

(፩) በተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው ወይም ይህንኑ ሰው በመወከል በባለቤትነት ወይም በይዞታነት የተያዘ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ሀብት፤

(፪) ለተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ ለተላለፈበት ሰው ወይም ለዚሁ ሰው ጥቅም ሲባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተደራሽ እንዲሆን የተደረገን ማንኛውም ሀብት፤

(፫) በተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ በተላለፈበት ሰው የተደረገን ማንኛውም የፋይናንስ ግብይት፤

ዓይነት፣ ባህሪ፣ መጠን ወይም ብዛት፡፡

፬/ ማዕከሉ መረጃ የሚቀርብለትን አኳኋን እና ጊዜ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ማዕከሉ በመመሪያ ጊዜውን ያልወሰነ ከሆነ የተጠየቀው መረጃ በተገቢ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

፮/ የመረጃ ጥያቄው ሁኔታዎች በተለወጡ ቁጥር ወይም ማዕከሉ በሚወስነው በመደበኛ ጊዜ መረጃዎች ለማዕከሉ እንዲደርሱ ለማድረግ የሚያስችል ቀጣይነት ያለውን ግዴታ ሊያካትት ይችላል፡፡

## ፲፯. ሰነድ ስለማቅረብ

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የሚጠየቅ መረጃ የተወሰኑ ሰነዶች ወይም ስለተወሰነ ነገር የሚገልጹ ወይም የሚዘረዝሩ ሰነዶች እንዲቀርቡ መጠየቅን ሊጨምር ይችላል፡፡

፪/ ማዕከሉ ሰነድ እንዲቀርብለት ሲጠይቅ፡-

ሀ) የሰነዱን ኮፒ ወይም የሰነዱ የተወሰነ ክፍል ለመውሰድ፤

ለ) ሰነዱን ያቀረበው ሰው ስለሰነዱ ገለፃ እንዲያደርግለት ሊጠይቅ፤

ሐ) ሰነዱን ያቀረበው ሰው የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ከሆነ የድርጅቱ ኃላፊ የሆነ ወይም የነበረ ወይም ሰራተኛ የሆነ ሰው ይህንኑ ገለፃ እንዲያደርግለት ሊጠይቅ፤

ይችላል፡፡

፫/ ማዕከሉ የተሰየመው ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰው ሰነድ እንዲያቀርብ የጠየቀ እንደሆነ ይህ ሰው፡-

ሀ) ሰነዱ አስቀድሞ በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር የሚገኝ ካልሆነ ሰነዱን ለማግኘት ተገቢ የሆነ ጥረት ማድረግ፤ እና

ለ) ለማዕከሉ ለመስጠት ካልሆነ ወይም ማዕከሉ በሌላ ሁኔታ ካልፈቀደ በስተቀር ሰነዱን በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር ጠብቆ ማቆየት፤

አለበት፡፡

(1) the type, nature, amount or quantity of any asset owned, held or controlled by or on behalf of a designated or convicted person;

(2) the type, nature, amount or quantity of any asset made available directly or indirectly to, or for the benefit of, a designated or convicted person; or

(3) the type, nature, amount or quantity of any financial transactions entered into by a designated or convicted person.

4/ The Center may, by issuing directive, specify the manner in which, and the period within which, information is to be provided.

5/ If no such period is specified in accordance with sub-article (4) of this Article, the information which has been requested shall be provided within a reasonable time.

6/ A request may include a continuing obligation to keep the Center informed as circumstances change or on such regular basis as the Center may specify.

## 17. Production of Documents

1/ A request under Article 16 of this Regulation may include a request to produce specified documents or documents of a specified kind or description.

2/ Where the Center requests that documents be produced, it may:

a) take copies of or extracts from any document so produced;

b) request any person producing a document to give an explanation of it;

c) where that person is a legal person, request any person who is a present or past officer of, or employee of, the legal person to give such an explanation.

3/ Where the Center requests a designated or convicted person to produce a document, that person shall:

a) take reasonable steps to obtain the document, if not already in the person's possession or control; and

b) keep the document under his possession or control except for the purpose of providing it to the Center or as the Center may otherwise permit.

## ፲፰. ስለመረጃዎች ሚስጥራዊነት

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬(፩) መሠረት በማዕከሉ መረጃዎች የሰጠው ሰው ወይም እነዚህን መረጃዎች ያገኘ ሰው ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ካልሆነ በስተቀር መረጃዎቹን ለሌላ ሰው መግለጽ የለበትም::

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ መረጃ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ለሌላ ሰው ተገለጸ ሊባል የሚችለው:-

ሀ) በዚህ ደንብ የተደነገገን ግዴታ ለመወጣት፤ ወይም

ለ) ማንኛውንም የክርክር ሂደት በሚመለከት የፍርድ ቤት ሥነ ሥርዓት ሕግን ለሟሟላት ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝን ለመፈፀም፤

ሲባልና ለዚሁ በሚያስፈልግ ደረጃ የተገለጸ እንደሆነ ነው::

፫/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም መረጃው ከሌላ ምንጭ አስቀድሞ ለሕዝብ ይፋ የተደረገ ከሆነ መረጃው የደረሰው ሰው መረጃውን እንዳይገልጽ አይከለከልም::

## ፲፱. መረጃን የመግለጽ ጠቅላላ ስልጣን

ማዕከሉ በዚህ ደንብ መሠረት ሥራውን ሲያከናውን ያገኘውን ማንኛውንም መረጃ፣ የቀረበለትን ሰነድ፣ የሰነዱን ኮፒ ወይም የሰነዱን የተወሰነ ክፍል ጨምሮ ለሚከተሉት ሊገልፅ ይችላል:-

፩) ኃላፊነት ላለበት ሰው እና አግባብ ላላቸው የመንግስት አካላት፤

፪) በዚህ ደንብ መሠረት የተወሰዱ እርምጃዎች ለሚመለከ ቷቸው አግባብ ላሏቸው የውጭ አገር መንግሥት አካላት::

## ፳. ከሕግ ውጪ መረጃን ስለመግለጽ

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት የቀረበ ወይም የተላለፈ መረጃን በሥራው አጋጣሚ ያወቀ ወይም የያዘ ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም ሲባል ካልሆነ በስተቀር መረጃውን፣ የመረጃውን ምንጭ ጨምሮ፣ በማናቸውም መንገድ መግለጽ የለበትም::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ክልከላ የግለሰቡ የስራ ግንኙነት ከተቋረጠም በኋላ ቢሆን የሚቀጥል ይሆናል::

## 18. Confidentiality of Information

1/ A person that is provided by the Center with information in accordance with Article 4(1) of this Regulation, or who obtains such information, shall not disclose it except with lawful authority.

2/ For the purpose of sub-article (1) of this Article, information is disclosed with lawful authority only if and to the extent that:

a) the disclosure is necessary to give effect to a requirement under this Regulation; or

b) the disclosure is required, under rules of court or a court order, for the purposes of legal proceedings of any description.

3/ Notwithstanding the provisions of this Article, any notified person may not be prevented from the disclosure of information that is already available to the public from other sources.

## 19. General Power to Disclose Information

The Center may disclose any information obtained in the exercise of its powers under this Regulation, including any document so obtained or any copy or extract made of such document:

1/ to the relevant competent authorities; and

2/ to the competent authorities in any foreign state concerned with measures taken under this Regulation.

## 20. Unlawful Disclosure of Information

1/ A person who in the course of his duties, knows or is in possession of any information submitted or exchanged pursuant to the provisions of this Regulation, may not disclose such information in any form whatsoever, including the disclosure of the source of the information except for the purpose of implementing this Regulation.

2/ The prohibition under sub-article (1) of this Article shall continue even after the termination of the relevant duties of a person.

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፩. ከተባበሩት መንግስታት ጋር ስለሚደረግ የግንኙነት መስመር

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት ከኮሚቴው ጋር በማዕከሉ የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት መተላለፍ አለበት፡፡

፪/ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት በቁጥር ፩ሺ.፪፻፷፯ (፲፱፻፺፱)፣ ፩ሺ.፫፻፴፫ (፪ሺ.)፣ ፩ሺ.፫፻፷፫ (፪ሺ.፩)፣ ፩ሺ.፫፻፸፫ (፪ሺ.፩)፣ ፩ሺ.፫፻፺ (፪ሺ.፪)፣ ፩ሺ.፬፻፶፪ (፪ሺ.፪)፣ ፩ሺ.፬፻፶፭ (፪ሺ.፫)፣ ፩ሺ.፭፻፳፮ (፪ሺ.፬)፣ ፩ሺ.፭፻፷፮ (፪ሺ.፬)፣ ፩ሺ.፮፻፲፯ (፪ሺ.፭)፣ ፩ሺ.፮፻፳፬ (፪ሺ.፭)፣ ፩ሺ.፮፻፺፱ (፪ሺ.፮)፣ ፩ሺ.፯፻፴ (፪ሺ.፮)፣ ፩ሺ.፯፻፴፭ (፪ሺ.፮)፣ ፩ሺ.፰፻፳፪ (፪ሺ.፰)፣ ፩ሺ.፱፻፬ (፪ሺ.፱)፣ ፩ሺ.፱፻፹፰ (፪ሺ.፲፩)፣ ፩ሺ.፱፻፹፱ (፪ሺ.፲፩)፣ ፪ሺ.፹፪ (፪ሺ.፲፪)፣ እና ፪ሺ.፹፫ (፪ሺ.፲፪)፣ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በማስፈጸም ሂደት የተወሰዱ እርምጃዎችን የሚመለከቱ አስፈላጊ ሪፖርቶችን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሪነት የፍትህ ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና ማዕከሉን በማካተት በኢትዮጵያ፣ በተባበሩት መንግሥታት እና በሌሎች አገራት ወይም ተቋማት ስምምነት ላይ በተደረሰበት የጊዜ ልዩነት ማዘጋጀትና ማቅረብ አለባቸው፡፡

### ፳፪. ዓለም አቀፍ ትብብር

፩/ ማዕከሉ በራሱ ወይም አግባብ ካላቸው ባለስልጣናት ጋር በመተባበር የተሰየመን ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ሀብት ወይም የፋይናንስ ግብይት በኢትዮጵያ ወይም በሌላ ቦታ በማገድ ወይም በመመርመር ሂደት በአዋጁ መሠረት ለመተባበር ተገቢ መስሎ የታየውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

፪/ የሽብር ተግባርን በገንዘብ መርዳትን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንፃር አገራት እርስ በርሳቸው ትብብር እንዲያደርጉ በሚደነግግ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት የውጭ አገር መንግስት፡-

ሀ) የሽብር ድርጊትን ያመቻቸ ወይም አሸባሪን ወይም አሸባሪ ድርጅትን በማቴሪያል የደገፈ ድርጅትን ጨምሮ በዚያ አገር የተሰየመ ሰው ሀብት፤

ለ) የተሰየመው ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባለቤትነት የያዘው ወይም የሚቆጣጠረው ድርጅት ሀብት፤

## PART FIVE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 21. Channel of Communication with United Nations

1/ Any communication required to be transmitted to the Committee under this Regulation shall be effected by the Center through the Ministry of Foreign Affairs.

2/ Under the lead of the Ministry of Foreign Affairs, the Ministry of Justice, the National Intelligence and Security Service, and the Center shall jointly prepare and submit necessary reports at such intervals as may be agreed between Ethiopia, the United Nations and other countries or relevant institutions, on the measures taken in Ethiopia in the course of application of the United Nations Security Council Resolutions No. 1267 (1999), 1333 (2000), 1363 (2001), 1373 (2001), 1390 (2002), 1452 (2002), 1455 (2003), 1526 (2004), 1566 (2004), 1617 (2005), 1624 (2005), 1699 (2006), 1730 (2006),1735 (2006), 1822 (2008) 1904 (2009), 1988 (2011), 1989 (2011), 2082 (2012) and 2083 (2012) and any other relevant Resolution of the Security Council.

### 22. International Cooperation

1/ The Center may, independently or in collaboration with other competent authorities, take such steps as it considers appropriate to cooperate with any freezing or investigation in Ethiopia or elsewhere, relating to the assets or financial transactions of a designated or convicted person as set out under the Proclamation.

2/ Where a foreign state, pursuant to a resolution by the United Nations Security Council calling on states to cooperate with one another in the prevention and suppression of the financing of any terrorist activity, requests Ethiopia to freeze:

a) the assets of person designated by it including organizations which facilitate terrorist activities or materially supports terrorists or terrorist organizations;

b) the assets of organization owned or controlled directly or indirectly by such person;

ሐ) የተሰየመው ሰው ወኪል በመሆን ወይም በዚሁ ሰው አመራር ሰጪነት ተግባሩን የሚያከናውን ሰው ሀብት፤

መ) የተሰየመው ሰው በባለቤትነት ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚቆጣጠረው ንብረት የተገኘ ወይም የመነጨ ፈንድ፤

እንዲታገድ ኢትዮጵያን የጠየቀ እንደሆነ አግባብ ባለው የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት የሕግ ድጋፍ የጋራ ትብብር ለማድረግ ጥያቄው ለማዕከሉ መቅረብ አለበት፡፡

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፰ እንደተጠበቀ ሆኖ የትብብር ጥያቄው የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

ሀ) ሀብቱ የሚታገድበት ሰው የሽብር ተግባር ስለመፈፀሙ ወይም ከሽብር ተግባር ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚያስረዱ ፍሬ ነገሮችን የሚዘረዝር መግለጫ፤

ለ) የሚታገደው ሀብት ከማንኛውም የሽብር ድርጊት ጋር የተያያዙ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎች ፍሬ ስለመሆኑ ወይም ለታቀዱ የሽብር ተግባራት በመሣሪያነት የሚውል ስለመሆኑ የሚያስረዱ ፍሬ ነገሮችን የሚዘረዝር መግለጫ፤

ሐ) እርምጃው የሚመለከተውን ሰው ማንነትና አድራሻ በበቂ ደረጃ ለመለየት የሚያስችል የተሟላ መረጃ፤

መ) የሚታወቅ ከሆነ በሀብቱ ላይ የይገባኛል መብት አለን የሚሉ ሰዎችን ማንነትና አድራሻ ከመብቶቻቸው ዓይነት ጭምር የሚያሳይ መግለጫ፤ እና

ሠ) የተሰየመውን ሰው በሚመለከት በጠያቂው አገር የተካሄደ፣ በመካሄድ ላይ ያለ ወይም ሊካሄድ የታሰበ የወንጀል ክስ ሂደቶችን ዝርዝር የሚያሳይ መግለጫ፡፡

፬/ ማዕከሉ ምክንያታዊ በሆኑ መሥፈርቶች ላይ ተመሥርቶ የትብብር ድጋፉ ሊሰጥ ይገባል ብሎ ካመነ የሚመለከተው ባለሥልጣን እንዲፈጽመው ወይም እንዲወስንበት በጥያቄው ላይ ያለውን አስተያየት ጨምሮ በተገቢው ጊዜ ውስጥ ያስተላልፍለታል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረግ የሀብት እገዳ የሚመለከታቸው ወገኖች በጋዜጣም ሆነ በማንኛቸውም መንገድ አስቀድሞ እንዲያውቁት ማድረግም ሆነ የወንጀል ምርመራ ማካሄድ ሳያስፈልግና ባለጉዳዮች በሌሉበት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

c) the assets of person acting on behalf of, or at the direction of such person;

d) funds derived or generated from property owned or controlled directly or indirectly by such person and associated persons;

such request shall be submitted to the Center for mutual legal assistance in accordance with the relevant United Nations Security Council Resolution.

3/ Without prejudice to Article 48 of the Proclamation, a request for assistance shall contain:

a) a statement detailing the facts on which it is believed that the person whose asset is to be frozen, is engaged in any terrorist activity, or associated with any terrorist act;

b) a statement detailing the basis on which it is believed that the assets to be frozen are either the proceeds of unlawful activities associated with any terrorist act, or instrumentalities of intended terrorist acts;

c) the full particulars of the person affected, to establish that person's identity and location with reasonable certainty;

d) where known, a reference to persons who may also have an interest in the assets and the nature of such interest, as well as particulars pertaining to the identity and location of said persons;

e) a statement detailing any criminal proceedings concluded, pending or contemplated against the person in the requesting country.

4/ The Center, if satisfied on a standard of reasonable grounds that such assistance be granted, shall, within a reasonable period, forward the request with such observations as it may make, to the competent authority for execution or its determination.

5/ Asset freezing under the provisions of this Article shall be enforced through an *ex parte* procedure without giving prior notification to the interested party concerned in any manner including by way of newspaper and without conducting a criminal investigation.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የሀብት ዕገዳ እርምጃ ከተወሰደ በኋላ ማዕከሉ እገዳውን በማረጋገጥ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፤ ሆኖም ማዕከሉ እገዳውን ለማረጋገጥም ሆነ ላለማረጋገጥ በሚወስንበት ሂደት ጠያቂው አገር ጥያቄውን ለመደገፍ ያቀረባቸውን መረጃዎች ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ አለበት፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የዕገዳ ትዕዛዝ ተፈፃሚ ከተደረገ ጠያቂው የውጭ መንግስት አካል የሀብት እገዳ ጥያቄውን ካላነሳ ወይም ማዕከሉ የእግድ ጥያቄው ተገቢነቱን እንደያዘ ያልቀጠለ መሆኑን ካልወሰነ በስተቀር ተፈጻሚነቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቀጥላል፡፡

፰/ የሀብት እገዳ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና(፮) መሠረት እስከተረጋገጠ ድረስ ጉዳዩ በዚህ ደንብ በተመለከተው "የተሰየመ ሰው" ሀብት የሚ ታገድበትን ስነ-ስርዓት በጠበቀ መልክ የሚስተ ናገድ ይሆናል፡፡

## ፳፫. ሀብትን መያዝና መውረስ

የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበት ሰውን ሀብት የመያዝ ወይም የመውረስ ስነ-ስርዓት አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፳፬. ሌሎች ኃላፊነት ያለባቸው አካላት

ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ሲባል የኢትዮጵያ ኢንቨስትመ ንት ኤጀንሲ፣ የንግድ ሚኒስቴር፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስ ቴርን እና ሌሎች ኃላፊነት ያለባቸው የመንግስት ተቋማት ሪፖርት በማቅረብ ረገድ በዚህ ደንብ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፮) በተመለከተው "ኃላፊነት ያለበት ሰው" ትርጓሜ እንደሚሸፈን ተደርጎ ይቆጠራሉ፡፡

## ፳፭. የመተባበር ግዴታ

፩/ ማንኛውም የሚመለከተው አካል ማዕከሉ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት ሥልጣንና ተግባሩን በሥራ ላይ ሲያውል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ማዕከሉ በራሱ ወይም በአዋጁ መሠረት አግባብ ካለው ባለስልጣን ጋር በመተባበር በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ የተመለከቱ ግዴታዎች ስለመፈፀማ ቸው አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

## ፳፮. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳፮ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

6/ The Center shall confirm the freezing under sub-article (5) of this Article and publish the same *ex post facto* on newspapers having wide circulation, provided, however, when considering whether to confirm or not the freezing, it shall take all appropriate measures to protect the confidentiality of the information provided by the requesting state in support of its request.

7/ If freezing order is enforced pursuant to the provisions of this Article, the duration of such freezing shall be indefinite until the foreign jurisdiction withdraws the request for assets to be frozen or until the Center decides that the freezing request no longer meets the standard of reasonable grounds.

8/ Once a freezing has been confirmed under sub-article (5) and (6) of this Article, the subject shall be considered to be covered under the definition of "designated person" as provided under this Regulation.

## 23. Seizure and Confiscation of Assets

Other relevant laws shall be applicable in the case of the procedure for seizure and confiscation of the assets of designated or convicted person in Ethiopia.

## 24. Other Accountable Persons

For the proper application of this Regulation, the Ethiopian Investment Agency, Ministry of Trade, the Ministry of Industry and other relevant government authorities shall be treated as "accountable persons" under Article 2(6) of this Regulation for the purpose of report submission.

## 25. Duty to Cooperate

1/ Every concerned body shall have the obligation to cooperate with the Center in exercising its powers and duties pursuant to the Proclamation and this Regulation.

2/ The Center shall, either independently or in collaboration with other competent authorities under the Proclamation, monitor a compliance with obligations stated under the Proclamation or this Regulation.

## 26. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of June, 2014.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**